# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---237498
ቀን- ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

**አመልካች:-** አቶ ካሳሁን አስፋዉ በየነ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ወርቅነሽ ደጀን ሀብቴ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍርድ</u>

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የፍርድ አፈጻጸምን የተመለከተ ጉዳይ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪ የፍ/ባለመብት ሲሆኑ አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 147947 ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 291757 ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ፡- ለአፈጻጸም ብይኑ መነሻ የሆነዉ አመልካች ሚያዚያ 03 ቀን 2014 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ለልጅ ቀለብ እንዲከፍሉ የተወሰነዉ በወር ብር 800 ሆኖ እንደማንኛዉም ቀለብ ከፋይ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በየወቀቱ ሊጠየቁ ሲገባ ንብረት ተሸጦ ከደረሳቸዉ ገንዘብ ላይ የልጅ ቀለብ ብር 200,000 ተቀንሶ በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት እንዲቀመጥ የተሰጠዉ ትዕዛዝ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲነሳላቸዉ መጠየቃቸዉ ነዉ፡፡ ተጠሪ ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ አመልካች በተደጋጋሚ ቀለብ የማይከፍሉ በመሆናቸዉ ገንዘቡ ከተለቀቀ የቀለብ ገንዘብ ማስከፈል የሚቻልበት ንብረት ስለማይኖር ገንዘቡ ሊለቀቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በበኩላቸዉ ብር 1,000 ጡረታ ስለሚከፈላቸዉ ገንዘቡ ቢለቀቅም ግዴታቸዉን እንደሚወጡ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና መርምሮ በፌዴራሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 36(2) መሰረት በሕጻናት ጉዳይ ዉሳኔ ሲሰጥ የሕጻናቱን ጥቅም ማዕከል ባደረገና ባስከበረ መልኩ ሊሆን እንደሚገባዉ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 45819 የልጆች ዕድሜ 18 ዓመት እስኪሞላ ድረስ ቀለብ ሰፋሪዉ ግዴታወን ሊወጣ የማይችል መስሎ ከታዬ ንብረት አግዶም ቢሆን ግዴታዉን እንዲወጣ ሊያደርግ የሚችል እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በሰጠዉ ትርጉም መሠረት አመልካች በተደጋጋሚ ቀለብ የማይከፍሉና ግዴታቸዉን ለመወጣት የሚያስችል ገቢ ወይም የገቢ ምንጭ የሌላቸዉ አዛዉንት በመሆናቸዉ የታገደዉ ገንዘብ ቢለቀቅ ሕጻኑ ቀለብ ሊያገኝ የሚችልበት መንገድ ችግር ዉስጥ ስለሚገባ ለሕጻኑ ጥቅም ሲባል አስቀድሞ የካቲት 16 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠዉ ትዕዛዝ መሠረት ብር 200,000 ተቀንሶና ተቀምጦ እየተቀነሰ ቀለብ ሊከፈል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተዉ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ብይኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

አመልካች ሕዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 3 ገጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- አመልካች ቀለብ ከሚከፍላት ልጃቸዉ በተጨማሪ የሚያስተዳድራቸዉ ቤተሰቦች ያሏቸዉ በመሆኑ ብር 200,000 ያህል እንዲታገድ መደረጉ የአመልካችን ኢኮኖሚ የሚያናጋና በቤተሰቦቻቸዉ በከፍተኛ ችግር ላይ እንዲወድቁ ያደረገ በመሆኑ ከተቻለ ዕግዱ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳና የልጅ ቀለብ ክፍያዉን በየወሩ እንዲከፈል እንዲደረግ፤ ይህ የማይቻልበት ሕጋዊ ምክንያት ካለ ልጁ በአሁኑ ወቅት 6 ዓመት ከ7 ወር ዕድሜ ላይ ስለምትገኝ 18 ዓመት እስኪሞላት የሚኖረዉን የ11 ዓመት ከ5 ወር የቀለብ ክፍያ ብር 109,600 ታግዶ ቀሪዉ ገንዘብ እንዲለቀቅላቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ከአሁን አመልካች የሚፈለገዉ የቀለብ ገንዘብ ቀለብ ተቀባይዋ አካለ መጠን እስክትደርስ ወይም 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ታስቦ መታገድ ሲኖርበት የአመልካችን ገንዘብ ሁሉ የመታገዱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ነዉ፡፡

ተጠሪ የካቲት 06 ቀን 2015 ዓ.ም ተዘጋጀ 1 ገጽ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡- አመልካች ሥራ ሰሩም አልሰሩ የቀለብ ገንዘብ መክፈል አይፈልጉም፤ ገንዘቡም ሊታገድ የቻለዉ አመልካች ቀለብ ገንዘቡን ስለማይከፍሉ ነዉ፡፡ ለልጅ ቀለብ በወር ብር 800 ተብሎ የተወሰነዉ ካለዉ የኑሮ ዉድነት ሁኔታ፣ የቤት ኪራይ መጨመር እና ልጅቷ ዕድሜዋ በጨመረ ቁጥር ፍላጎት ስለሚጨምር ገንዘቡ በቂ ባለመሆኑ ቀለብ ይጨመር ጥያቄ አቅርበዉ በቀጠሮ ላይ በመሆኑና አቤቱታቸዉ ተቀባይነት ቢያገኝ አመልካችን ሊያገኙ ስለማይችሉ ቀለብ ይጨመር አቤቱታ ላይ ዉሳኔ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ በመዝገቡ ላይ ዉሳኔ ሳይሰጥ እንዲቆይ የሚጠይቅ ነዉ፡፡ አመልካች የካቲት 15 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀ 2 ገጽ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት የአፈጻጸም ብይን እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ምላሽ የሚያሻዉ ጭብጥ ከአሁን አመልካች የሚፈለገዉ የቀለብ ገንዘብ ቀለብ ተቀባይዋ አካለ መጠን እስክትደርስ ወይም 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ታስቦ መታገድ ሲኖርበት የአመልካችን ገንዘብ የሆነዉ ብር 200,000 በሙሉ መታገዱ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ አንድን ፍርድ ለማስፈጸም የፍርድ ባለዕዳዉን ንብረት ማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፍርድ ባለዕዳዉ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ተከብሮ እንዲቆይና ለፍርዱ አፈጻጸም እንዲዉል ሊደረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 379 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በተለይ ከፍርድ በፊት በክርክር ሂደት ንብረት ተከብሮ እንዲቆይ የሚሰጠዉ ትዕዛዝ፣ ወይም ፍርድ አርፎም ቢሆን የዕዳዉ መክፈያ ገና ወደፊት የሚመጣ ሲሆን ለአፈጻጸም ሊዉል የሚችል ንብረት የሚሸሽ ወይም የሚባክን መሆኑ ሲታመንበት የሚከበረዉ ወይም የሚያዘዉ ንብረት ከሚወሰነዉ ወይም ተወስኖ የመክፈያዉ ጊዜ ገና ከሆነዉ ዕዳ ጋር ተመዛዛኝ መጠን ያለዉ ሊሆን እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 151 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ በተለይ የሕጻናትን ቀለብ አስመልክቶ ቀለብ እንዲከፍል የተወሰነበት ሰዉ በየጊዜዉ እንዲከፍል የተወሰነበትን የቀለብ ገንዘብ ጊዜዉ ደርሶ ካልከፈለና ለወደፊቱም የማይከፍል ሲመስል የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ተከብሮ ለቀለብ ክፍያ እንዲዉል ማድረጉ የሕጻናትን መብት ከማስከበር አኳያ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 45819 የመክፈያ ጊዜዉ ገና ለሆነዉ የቀለብ ገንዘብ አከፋፈል ጭምር የቀለብ ከፋዩን ንብረት አስከብሮ መያዝ እንደሚቻል ገዥ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ሆኖም የሚያዘዉ ወይም የሚከበረዉ ገንዘብ ከዕዳዉ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል፡፡ ተመጣጣኝ ካልሆነ የተከበረዉን ንብረት ወይም ገንዘብ በከፊል ከእገዳ ነጻ በማድረግ ማመዛዘኑ ተገቢ ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች በየወሩ እንዲከፍሉ የተወሰናባቸዉን ብር 800 የልጅ ቀለብ ጊዜዉን ጠብቀዉ ባለመክፈላቸዉና ለመክፈልም ሌላ በቂ የገቢ ምንጭ ያላቸዉ መሆኑን ባለማስረዳታቸዉ ከቤት ሽያጭ ድርሻቸዉ ብር 200,000 ተከብሮ እንዲቆይና መክፈያዉ የደረሰዉ የቀለብ ክፍያ ዉጪ እየሆነ እንዲከፍል በስር ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች አጥብቀዉ የሚከራከሩት ከተቻለ ዕግዱ ሙሉ በሙሉ ተነስቶላቸዉ የልጅ ቀለብ ክፍያዉን በየወሩ እንዲከፍሉ እንዲታዘዝላቸዉ ሲሆን ካልተቻለ ግን የቀለብ ተከፋይ ልጃቸዉ የወቅቱ ዕድሜ 6 ዓመት ከ7 ወር በመሆኑ 18 ዓመት እስኪሞላት ያለዉ የ11 ዓመት ከ5 ወር ቀለብ በወር በብር 800 ተሰልቶ የሚመጣዉ ብር 109,600 ተከብሮ እንዲቆይና ቀሪዉ ገንዘብ ላይ ያለዉ ዕግድ እንዲነሳላቸዉ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸዉ የሚከራከሩት አመልካች ቀለብ ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዉ በማቋረጣቸዉና ሌላ በቂ የገቢ ምንጭ የሌላቸዉ በመሆኑ የተሰጠ ዕግድ በመሆኑ እንዲሁም የልጅቱ ዕድሜ እየጨመረ ሲመጣ ፍላጎቷ ከመጨመሩ አንጻር የልጅ ቀለቡ እንዲከለስና እንዲጨመር ጥያቄ ቀርቦ በሂደት ላይ ያለ በመሆኑ ቀድሞ በነበረዉ በወር ብር 800 ሂሳብ ብቻ ተሰልቶ ሊስተካከል አይገባም በሚል ነዉ፡፡ ከላይ ከተገለጸዉ መነሻነት የሕጻኗን ሕገ-መንግስታዊ መብት ከማስከበርና ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 45819 የወደፊት የሕጻኒቱ የቀለብ ጥያቄ አከፋፈል ዋስትና ከማስጠበቅ አንጻር የስር ፍ/ቤት ገንዘብ ተከብሮ ወይም ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ መስጡት የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል በየወሩ እንዲከፈል ከተወሰነዉ የቀለብ መጠን አንጻር የተከበረዉ ገንዘብ ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል የሚለዉን የአመልካች ጥያቄ በተመለከተ በርግጥ ተጠሪ እንደሚሉት በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 231/92 አንቀጽ 203 መሠረት በቀለብ ሰጪዉ ወይም በቀለብ ተቀባዩ ጥያቄ መነሻነት የቀለብ መጠን ሊሻሻል የሚችል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የተወሰነዉ ቀለብ ለቀለብ ተከፋዩ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለቀለብ ከፋዩም ጥቅም ጭምር ሊሻሻል የሚችል በመሆኑ የቀለቡ መጠን ገና ለገና የቀለብ ክፍያዉ ተሻሽሎ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሊወሰን ይችላል በሚል ግምትና ገንዘቡ ታግዶ የሚቆየዉ ለወደፊት የሕጻኗ ዕድሜ 18 እስኪሞላ ድረስ ተከፋይ የሚደረግ ቀለብ ጭምር መሆኑን ታሳቢ ባላደረገ መልኩ ተመጣጣኝ ያልሆነ የአመልካችን ገንዘብ አግዶ ማቆየቱ ተገቢ አይሆንም፡፡ የስር ፍ/ቤት የሕጻኗ አካለ መጠን እስኪሞላት ድረስ ለቀለብ አከፋፈል ዋስትና ይሁን ዘንድ ገንዘቡ ተከብሮ እንዲቆይና መክፈያ ጊዜዉ ሲደርስ ወጪ እየሆነ እንዲከፈል ብይን መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም በግራ ቀኙ በኩል ያለዉን አቅም፣ እየተከፈለ ያለዉን የቀለብ መጠንና ገንዘቡ ተከብሮ የሚቆይበትን ጊዜ ግምት ዉስጥ በማስገባት ተከብሮ የሚቆየዉን ገንዘብ መጠን ተመጣጣኝ አለማድረጉ ወይም አለማመዛዘኑ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም ተከብሮ ሊቆይ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን አሁን በየወሩ እንዲከፈል ከተወሰነዉ ብር 800 አንጻር ሕጻኗ አካለ መጠን እስክትደርስ ድረስ ያለዉ የ11 ዓመት ከ5 ወር ጊዜ ተሰልቶ የሚመጣዉ ብር 109,600 ሆኖ ቀሪዉ ብር 90,400 ከዕገዳ ነጻ ሆኖ ለአመልካች ሊለቀቅ የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለል በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ብይን በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 147947 ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 291757 ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ የአፈጻጸም ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ለቀለብ ክፍያዉ ተከብሮ የሚቆየዉ የገንዘብ መጠን ከሚከፈለዉ የቀለብ ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ሊደረግ ወይም ተመዛዛኝ ሊሆን ስለሚገባዉ ተከብሮ እንዲቆይ ከተባለዉ ብር 200,000 ዉስጥ ብር 109,600 ተከብሮ እንዲቆይ ተደርጎ ቀሪዉ ብር 90,400 ከዕገዳ ነጻ ሆኖ ለአመልካች ሊለቀቅላቸዉ ይገባል ተብሎ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡
3. ሌላዉ የስር ፍ/ቤት የአፈጻጸም ብይኑ ክፍል አልተነካም፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ዕ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !